


# ቴዲ እና የክሡ ፖለቲካዊ እንድምታ /ገ/ፃዲቅ አበራ/

በቴዲ አፍሮ ላይ የተመሠረተው ክስ፣ ቀጥሎም ዋስትና በመከልከል ወህኒ ቤት እንዲቆይ የተደረገበት ሒደትና ይህንን ተ ከትሎም በተለያዩ ወገኖች የተሠጡ አስተያየቶች እንዲሁም የግንቦት 13ቱ የምስክርነት ሂደት ለዚህ ፅሑፍ መነሻ ሆነዋል፡፡ ጉዳዩ ፖለቲካዊ ነው- አይደለም የሚለውም በራሱ እያነጋገረ ያለ ሲሆን፣ ከስሜት ባሻገር በተጨባጭ የሚታዩ ፖለቲካዊ እንደምታዎችን በዚህ ፅሑፍ ለመፈንጠቅ እሞክራለሁ፡፡

ቴዲ አፍሮ በሙዚቃው ብንወድውም፣ በስብዕናው ብናከብርውም፣ ለሐገሩና ለወገኑ ባለው ቀናዒነት ታላቅ ስፍራ ብንሠጠውም ተገጭቶ የሞተውም ወገናችን፣ የእኛው ዜጋ ስለነሆነ ብቻ ሣይሆን ሠው በመሆኑ እንቀረቀርለታለን፤ ከዚህም በተጨማሪ ሁላችንም ከህግ በታች መሆናችንም መረጋገጥ ይኖርበታል፤ቴዎድሮስ ካሣሁን ዝነኛ ስለሆነና ሚሊዮን አፍቃሪ ስላለው፣ ሟቹ ደግሞ ምንም ወገን ስለሌለው ደሙ ደመ ከልብ እንዲሆን በፍፁም ልንፈቅድ አይገባም፤ እኔ በግሌ ቴዲን ከልብ የምወደው ብቻ ሣይሆን፣ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ እስከ ዛሬ ያልታየ፣ እግዚአብሔር ችሎታን ከትህትና፣ ከዕውቀትና ከእምነት ጋር አቀራኝቶ የለገሠው ነው ብዬ አምናለሁ፡- ይህም ሁሉ ቢሆን ለሕግ የበላይነት መከበር ፣ ለሠብዓዊ ፍጡር ክብር ሲባል በቴዲ ላይ በነፃ ፍ/ቤት የሚሠጥን ውሳኔ መቀበል አማራጭ የሌለው ይሆናል፡፡

ለሠው ልጅ ያለኝ ክብር፣ ለሕግ የበላይነት ያለኝ አቋዋም ከላይ የተመለከተው ቢሆንም፣ በርግጥም ድርጊቱ በቴዎድሮስ ካሣሁን ተፈፅሟል ወይ? የሚለውን መመርመር የግድ ይለናል፡፤ ቴዎድሮስ ካሣሁን ጥቅምት 23/1999 ከለሊቱ 7:10 ቤተመንግስት አካባቢ /ፊት በር/ የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 2-59869 በሆነው የግል ተሽከርካሪው ደጉ ይበልጣል የተባለውን የጎዳና ተዳዳሪ ገጭቶ ስለመግደሉ፣ እና እርዳታ ሣያደርግለት ስለመብረሩ ዓቃቤ ህግ በክስ ማመልከቻው ላይ አስፍሯል፡፡ አደጋው በተከሠተ ማግስት ቴዎድሮስ ካሣሁን አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ቀርቦ፣ ከአንድ ቀን እስራት በኂላ በ50ሺህ ብር በዋስትና መፈታቱ ተዘግቧል፣ ቴዲ አፍሮ በዕለቱ እንኳን ሠው መግደል፣ አደጋው ደረሠ በተባለበት በአራት ኪሎ አካባቢ አለማለፉን በወቅቱ ለሚዲያዎች ከመግለፁ ባሻገር፣ ድርጊቱ ሲፈፀም በስፍራው የነበረና ቴዎድሮስ ካሣሁን ነው ድርጊቱን የፈፀመው የሚል ምስክር አልነበረም፤ በወቅቱ ቴዲ አፍሮን ይዘው ለማሠር እንደ ምክንያት የተጠቀሰውና ከእንግሊዘኛው ፎርቹን ጋዜጣ ዘገባ መረዳት የተቻለው፣ አንድ የማይታወቅ /ማንነቱን ያልገለፀ/ የታክሲ ሾፌር፣ አደጋውን ያደረሰው ተሽከርካሪ ይህ ነው ብሎ በስልክ ለፖሊስ በሠጠው ጥቆማ መሠረት ነው፡፡ የተ ባለው የታክሲ ሾፌር በርግጥ ደውሎ ለፖሊስ ነግሯል ወይ? በርግጥስ የታክሲ ሾፌር በሥፍራው ነበርን? ያ አደጋው ሲደርስ አየሁ ያለውና የሰሌዳ ቁጥር ለፖሊስ ሠጠ የተባለው የታክሲ ሾፌር ማንነቱን መደበቅ ለምን አስፈለገው? ዛሬ የዓይን ምስክር ነን የሚሉ ፖሊሶች ከየት መጡ? ክሱ ሲመሰረት ፕላን ሲነሳ የተመለከቱ የተባሉት ምስክሮች እንዴት ወደ ዓይን ምስክርነት ተለወጡ? አንደኛው ምስክር የተባለው ፖሊስ ኮንስታብል ክንፈ ስዩም ሞላ የት ደረሰ? የግድ በውሸት መስክር ተብሎ አልመሰክርም በማለቱ አፈኑት ወይንስ ገደሉት?ወይንስ ራሱ ፈርቶ ጠፋ? ለምስክርነት የተገኙትስ ያላዩትን የመሰከሩት የርሱ ዕጣ እንዳይደርሳቸው ፈርተውስ ቢሆን? በውሸት ማስመስከር በኢትዮጵያ የአቃብያን ህጎች መለያ ከሆነ አመታት የተቆጠሩ ሲሆን፣ያለማስረጃ የሚፈርዱ ዳኞችም በሽ ናቸው፡፡

ቴዎድሮስ የጎዳና ተዳዳሪ ገጭቶ ስለመግደሉ ይቅርና፣ በስፍራው እንኳን ስለማለፉ የሚያሳይ ምንም መረጃ በሌለበት አቃቤ ህግ ክስ መመስረቱን ከተያያዙት የዓቃቤ ህግ ማስረጃዎች መረዳት የተቻለ ሲሆን፣ ለአንድ

ሠዓት እንኳን በእስር ቤት መቆየት የማይገባውን ወጣት ድምፃዊ፣ ያለ ምንም ማስረጃ ፍ/ቤቱ ዋስትና እንደነፈገው የተያያዙትን ማስረጃዎች በመፈተሽ መረዳት ይቻላል፤ቴዎድሮስ ካሣሁን ሚያዚያ 8/2000 ለመጀመሪያ ጊዜ ፍ/ቤት በቀረበ ዕለት ከተነበበውና በኋላም ፍ/ቤቱ ሰኞ ሚያዚያ 13/2000 በሠጠው ብይን ተ ሻሽሎ ሚያዚያ 17 ከቀረበው ክስ ቻርጅ ጋር የተያያዙት ማስረጃዎች አደጋው ከቴዲ አፍሮ ጋር ስለመያያዙ የሚያስረዱ አይደሉም፤እንመልከታቸው፡-

ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸው ማስረጃዎች በሙሉ የሚከተሉት ናቸው::

## ሀ. የሠው ማስረጃ

1. ኮንስታብል ከበደ ወየሣ ጉዳታ
   አድራሻ አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 08 የቤት ቁጥር----- ቀበሌ አዳራሽ
2. ኮንስታብል ታምራት ዶላ ከቤሮ
3. ኮንስታብል ክንፈ ስዩም ሞላ- ጃንሜዳ ማዘዣ ጣቢያ
4. ኮንስታብል ጌትነት መርኔ /የፕላን ምስክር/
   አድራሻ አ/አ የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13/14 የቤ/ቁ.401

## ለ. የፅሑፍ ማስረጃ

1. ሟች ላይ የደረሠውን አደጋ የሚያሣይ ፎቶግራፍ -1 ገፅ
2. ሟች የተገጨበት ቢ.ኤም.ደብሊው የሠ.ቁጥር 2-59869 - አ/አ አውቶሞቢልን የሚያሳይ ፎቶግራፍ -1 ገፅ
3. ከዳግማዊ ምሊኒክ ሆስፒታል የተሠጠ የአስከሬን ምርመራ ውጤት -1 ገፅ
4. አደጋው የደረሠበትን ቦታ የሚያሳይ የትራፊክ ፕላን -2 ገፅ
5. የአውቶሞቢሉ የቴክኒክ ምርመራ ውጤት -1 ገፅ

በቃ! የቀረቡት ማስረጃዎቹ እነዚህ ናቸው፤ 4ቱ የሠው ምስክሮች የትራፊክና የፀጥታ ፖሊስ አባላት ሲሆኑ፣ የአንዱ ምስክርነት አደጋ ደረሠ በተባለበት ስፍራ ፕላን ማንሣቱን ለማስረዳት ሲሆን፣ ሦስቱ ደግሞ ፕላን ሲነሣ ያዩ የአይን ምስክሮች መሆናቸው ነበር በቅድሚያ በአቃቤ ህግ የተገለፀው፤በዚህም መነሻነት የቴዲ ጠበቃ ምስክሮቹ የአይን ምስክሮች ስላልሆኑ ደንበኛቸው በዋስ እንዲለቀቅ ጠየቁ፤የአቃቤ ህግ መከራከሪያ የነበረው በእንደዚህ አይነት አንቀፅ የሚከሰሱ ዋስትና ተፈቅዶላቸው አያውቅም የሚል ነበር፤አደጋው በደረሠበት ስፍራ አደጋውን ያደረሰው ተሽከርካሪ በሌለበት፣ ማን አደጋውን እንዳደረሠ በማይታወቅበት፣ ፕላን አንስተናል፣ ፕላን ሲነሣ ተመልክተናል የሚሉ ምስክሮች ድርጊቱ ከቴዎድሮስ ካሣሁን ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ምንም የሚሠጡት መረጃ እንደማይኖር እየታወቀ ቴዲ ዋስትና ከተከለከለ በኋላ ኣቃቤ ህግ ምስክሮቹ የአይን ምስክሮች ናቸው በማለት በጋዜጦች መግለጫ መስጠት ጀመረ፤ከዓመት በላይ የመረጃ ምንጭ ተደርጎ ሲጠቀስ የነበረው ማንነቱ የማይታወቅ የታክሲ ሾፌር እንደነበርም ይታወሳል፤

የፅሑፍ ማስረጃዎቹንም በተመለከተ በተራ ቁጥር 1 የሠፈረው በሟች ላይ አደጋ እንደደረሠ የሚያሳይ ነው፤ ክርክሩ ግለሠቡ ሞቷል አልሞተም የሚል ባለመሆኑ ገዳዩን ከቴዎድሮስ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም::

2. በተራ ቁጥር 2 የተመለከተውም የቴዲ አፍሮን መኪና ፎቶግራፍ ከማያያዝ ውጭ በዚያ መኪና ግጭት ስለመፈፀሙ የሚያሳየው ነገር የለም::

3. በሶስተኛ ደረጃ የተመለከተውም የአስከሬን ምርመራ ውጤት ግለሠቡ ተገጭቶ አልሞተም የሚል ክርክር ባልተነሣበት፣ ጥያቄው ማን ገጨው የሚለው ምላሽ የሚፈለግ በሆነበት፣ ከቴዎድሮስ ካሣሁን ጋር ሊያይዘው የሚችል ነገር የለም::

4. በ5ኛ ደረጃ የተቀመጠው የቴዎድሮስ መኪና የቴክኒክ ምርመራና ውጤትም፣ ቴዎድሮስ ሠው ገጭቶ

መግደሉን የሚያረጋግጥ ሊሆን አይችልም፤ የተሽከርካሪው ምርመራ ውጤት በመኪናው ላይ ግጭት ስለመፈፀሙ ቢገልፅ፣ ይህ ግጭት በዕለቱ ሲኤምሲ አካባቢ ቴዎድሮስ ካሣሁን ከደረሠበት በግልፅ ከሚታወቀው ግጭት የተለየ ቢሆን እንኳን፣ በመኪናው ላይ የግጭት ምልክት በመታየቱ ብቻ፣ ግጭቱ ከግድያው ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ ምንም ጠቋሚና አጋዥ መረጃ በሌለበት የሚሰጠው ፋይዳ አይኖርም።ዓቃቤ ህግ ያቀረባቸው ማስረጃዎች በቃ! እነዚህ ናቸው፤ ዓቃቤ ህግ ተከሣሽ ላይ ዋስትና የሚከለክል አንቀፅ ከመክፈት ውጭ ዋስትና ሊያስከለክል የሚገባ፣ ከድርጊቱ ጋር ስላለው ግንኙነት የሳሳ ክር እንኳን ማሣየት ባልቻለበት ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ሶስት አራት ቀጠሮ መሥጠቱ ሲገርመን ማክሰኞ፣ ሚያዚያ 21/2000 ዋስትና መከለከሉ፣ ስለ ኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ሲነገር የነበረውን ይበልጥ ግልፅ ያደረገ ክስተት ነው፤የምስክርነት ሂደቱ ደግሞ ይበልጥ ብዙ ይናገራል፤ ቴዲ ለምን በህግ ሽፋን የጥቃት ሰለባ ሆነ ?

ቴዲ በዚህ ሥርዓት በአፈንጋጭነት መፈረጅ የጀመረው፤ አንደንዶች «ግርማዊነትዎ» በሚለው ቁጥር አንድ የአቡጊዳ አልበሙ እንደሆነ ሲጠቅሡ፣ ብዙዎች እንደሚያምኑት ቴዲ በመንግስት ሠዎች በጥላቻ አይን መታየት የጀመረው በዝነኛው «ያስተሰርያል» አልበሙ ነው:: ቴዲ ግንቦት 8/97 በለቀቀው በዚህ ዝነኛ አልበሙ እጅግ መወደዱና በሕዝብ ውስጥ ታላቅ ሥፍራን መጎናፀፉ፣ ሥልጣን ላይ ባሉት ወገኖች ግን ቅሬታን አስከትሏል፤በገዢው ሰፈር ያሉት የጥላቻቸው መንስኤ ምናልባት በአንድ በኩል ምርጫው በተካሄደ ማግስት ይህን ዝነኛ አልበሙን በመልቀቁና ሕዝባዊ ተቃውሞው ማየሉን አንድም በ«ገደቢስነት» አይተውት፣ አሊያም ሙዚቃው፣ ለህዝቡ መነሣሣት ሚና አለው ብለው ገምተውት ሊሆን ይችላል፣ «ኢፍቲን» በተባለው አፍቃሬ ኢሕአዴግ ጋዜጣ ላይ ቴዎድሮስ ካሣሁን «በያስተሰርያል» ሊከሰስ መሆኑ በሐምሌ 97 ተዘግቧል፣

እንዲሁም በመንግስት ሚዲያዎች እንዳይተላለፉ ገደብ ከተጣለባቸው የቴዲ አፍሮ ዘፈኖች እንዱ ያስተ ሰርያል የሚለው ነው፤ ይህን ዘፈን ለ1998 ዘመን መለወጫ በሸራተን አዲስ ቴዲ እንዳይዘፍን አስቀድሞ በመወሠኑ እሱ ደግሞ፣ «ስለ እርቅ፣ ስለመቻቻል» ያቀነቀንኩት ካልተሠማልኝ በፕሮግራሙ አልገኝም ብሎ ውሉን ማቋረጡና የ130 ሺህ ብር ስምምነቱን መሰረዙ አይዘነጋም፤ቴዲ አፍሮ የማይሣተፍ ከሆነ በማለት ጥቂት የማይባሉ ሠዎች የገዙትን ትኬት በመመለስ ገንዘባቸውን ተቀበሉ፤ ቴዲ በዚህ ርምጃው በ«ሼሁ»ና በመንግስት ወገኖች ዘንድ ጥላቻና ቂምን አትርፎበታል፤ በጥቅምት 98 በአዲስ አበባ ግድያ በነገሠበት ወቅት በአሜሪካ በአንድ መድረክ የነበረውን የሙዚቃ ኮንሠርት በመሠረዝ ሀዘኑን መግለፁም ግድያውን ለፈፀሙት ገዢዎች የሚያስደስት አልነበረም፤ጠ/ሚ/ሩ ባሉበት በሚሊኒየሙ ዋዜማ በሚሊኒየም አዳራሽ ከተሣተፉት ድምፃውያን ውስጥ ሳይገኝ፣በጃንሜዳና በስታዲየም መዝፈኑም እንደ ድፍረት ተቆጥሮበታል።ገብረ ኪዳን ደስታ የተባሉ የሥርዓቱ አቀንቃኝ በ1998 ባሳተሙት «የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትናንት እስከዛሬ » በተባለው ዘረኛ መፅሀፋቸው በትምክህኝነትና በዘረኝነት ከፈረጁዋቸው ኢትዮጵያውያን አንዱ ቴዲ አፍሮ ነው፤ በመፅሀፉ በገጽ 239 እና 240

«በአስራ ሰባት መርፌ በጠቀመው ቁምጣ
ለለውጥ ያጎፈረው ዙፋን ላይ ከወጣ
እንዳምናው ባለቀን የአምናውን ከቀጣ
አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ »

የሚለውን የግጥም ስንኝ ከጠቀሱ በኋላ «ቴዲ አፍሮ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች አስራ ሰባት ዓመት ሙሉ እምቢ ለጭቆና ብለው የሞት ሽረት ትግል በማካሄድ የከፈሉትን ክቡር መስዋትነትና የተጎናፀፉትን ብሄራዊና ሀገራዊ መብትን ነው ትርጉም የለሽ ነው እያለን ያለው፤ለኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች መብትና ህልውና ሲሉ የህይወት መስዋዕትነት በከፈሉት ጀግኖችና ህዝቦች ላይም ከመሳለቅ አልተቆጠበም፤ደማቸው ደመ ከልብ ነው እያለን ነው» ሲሉ ፅፈዋል፤

ስማቸው በኖ.ረኝም፣ ለጊዜው ስማቸውን የማልጠቅሰው ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለሥልጣን በሚሊኒዬሙ በዐል ሰሞን ቴዲን ሊያገኙት መሞከራቸውና አብረው መታየታቸውን የቅርብ ምንጮች ይገልፃሉ፤ ከኢህአዴግ ባለሥልጣናት ውስጥ እጅግ በከፍተኛ ደረጃ በሕዝብ የሚጠሉ ሠው ቴዲን ማግኘታቸው እሳቸው ስለቀረቡት ስለ ሐገሩ፣ ስለ ወገኑ፣ መጨነቁን ይተዋል፣ ጡቷና ከንፈሯ ብቻ እያለ ያላዝናል የሚል ግምት በአንድ በኩል፣ በሌላም በኩል ይህ ባይሣካ እንኳን ቴዲ ከእኚህ ከፍተኛ ባለስልጣን ጋር መታየቱ በሕዝብ ዘንድ ይጠላል የሚል አማራጭም የተያዘ ይመስላል፤ከዚህ በኋላ ነበር በመንግስታዊው ኤፍኤም 97.1 ሬዲዮ የሙዚቃ ስራዎቹን በማብጠልጠል ተቀባይነቱን ለመሸርሸር የተሞከረው፡፡ይህ በሠይፉ ፋንታሁን መሪነት የተጀመረው ዘመቻ በሒደት እንደታየው በተጨበጡ መረጃዎች ላይ አለመመስረቱ ብቻ ሣይሆን ተከታታዮቹ ሂደቶች እንዳመለከቱት ሰይፉ በፍላጐቱ እንዲህ ያለ ጣጣ ውስጥ እንዳልገባ መገመት ይቻላል፤ ይህን ውዝግብ ተከትሎ በቴዲ ላይ አንድ አመት ከስድስት ወር የቆየ ጉዳይ መቀስቀሱና ሂደቱ ወደ መደበኛ ችሎት ማምራቱ የአጋጣሚ ነው ብሎ ለመደምደም በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ፣ ስልጣን ላይ ያለውን ቡድን ፍላጐት አለመገምገም ብቻ ይሆናል፡፡

ጉዳዩ ፖለቲካዊ ነው፤ ፖለቲካዊ አይደለም የሚለውን ለመመለስ የማስረጃ ክብደትና ቅለቱን በመመዘን ብቻ ሳይሆን ፣የበፊቱን ትተን ከክሱ አመሰራረት ጀምሮ ያለውን ሂደት ብቻ በመቃኘት ነገሩን ይበልጥ መ ረዳት ይቻላል፤ የቴዲን ጉዳይ በዳኝነት እንዲመሩ 8ኛ ችሎት የተሰየሙት አቶ ልዑል ገ/ማርያም፣ ፖለቲካዊ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን በመመልከት የታወቁ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ በኦነግ፣ በቅንጅትና በሌሎችም ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ ክሶችን በከፍተኛ ፍ/ቤት 5ኛና 2ኛ ወንጀል ችሎት ሲመሩ ቆይተዋል፤ የቅንጅት መሪዎችንም ክስ በቀኝ ዳኝነት የመሩ በሥርአቱ እምነት የሚጣልባቸው ሲሆን፤ በአንፃሩ በተከሳሾች ዘንድ ነፃ አይደሉም ተ ብለው በስፋት የሚጠቀሱም ሰው ናቸው፡፡ አሁን የትራፊክ ጉዳይ ወደሚታይበት ወደዚህ ችሎት እኚህ ዳኛ ሲመጡ፣ ጉዳዩ ፖለቲካዊ ስለመሆኑ አንድ ጠቋሚ ነው የሚል እምነት ካደረባቸው ዜጐች አንዱ ነኝ፤ እኝህ ሰው እስከ ሐምሌ 9/99 ዓ.ም የቅንጅት መሪዎችን ጉዳይ በቀኝ ዳኝነት ሲከታተሉ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ ከዋናው ፋይል የተነጠሉ ተከሳሾችን ጉዳይ እስከ ሐምሌ 30/99 ዓ.ም ከዚያም በኋላ በአዲሱ አመት በ2000 ዓ.ም መጀመሪያ የዳንኤልና የነፃነትን ጉዳይ ሲከታተሉ ነበር፤ በመሃል ታመው ከዚያም ለህክምና ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄደው እንደተመለሱ የተመደቡት አሁን የቴዲ ጉዳይ በሚታይበት 8ኛ ወንጀል ችሎት ነው፡፡ ይህ ችሎት በአንድ ዳኛ ብቻ የሚመራ የትራፊክ ክስ በብቸኝነት የሚታይበት ነው፡፡ የቴዲ የትራፊክ ክስ ቢያንስ በታህሳስ 2000 ዓ.ም መንቀሳቀሱን ከሳሽ አቃቤ ህጉ ለጋዜጦች ከሰጡት መግለጫ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ጊዜ ደግሞ አቶ ልዑል ወደዚህ ወደ አዲሱ ችሎት ከመመደባቸው በፊት ነው፤ ይህም የቴዲ ጉዳይ ወደ ፍ/ቤት መመራቱ ከታወቀ በኋላ፣ አቶ ልዑል ወደዚህ ችሎት መመደባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ቴዲ ወደ ወህኒ ቤት ሲወሰድ በቀጥታ ወደ ዞን 6 መወሰዱ፤ ይህ ደግሞ ከአስቀያሚው ቃሊቲ ወህኒ ቤት ይበልጥ አስከፊው ስፍራ ሲሆን፣ እዚህ የሚታሰሩት አደገኛ ቦዘኔ ተብለው የተፈረጁ ዜጐች ናቸው፤ በዚህም ስፍራ በአደገኛ ቦዘኔነት የሚጠረጠሩ ዜጎች ውጪ የሚታሰር ቢኖር በወህኒ ቤቱ ሃላፊዎች አይን በእስር ቤት ቆይታቸው ከፍተኛ ጥፋት ፈፅመዋል ተብለው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡አዲስ እስረኛ ለ15 ቀን ያህል የሚቆየው ዞን 3 በተባለው ቦታ ሲሆን፣ ከ15 ቀን በኋላ፣ ከዞን 6 ውጭ ባሉት ዞኖች ይበተናል፤ ቴዲ ግን በቀጥታ ዞን 6 ነበር የገባው፤ ይህ ለመጉዳትና ቅስሙን ለመስበር የታለመ ፖለቲካዊ ርምጃ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በኋላ በቀናት ውስጥ ከዞን 6 የወጣውም በአደገኛ ቦዘኔነት የታሰሩ ዜጎች ባሣዩት ፍቅርና ክብር ዋስትና ሲከለከል ሊረብሹ ይችላሉ በሚል እንደሆነም መገመት ይቻላል፤ ይህ ዞን ከሁሉም ዞኖች ይበልጥ ሃይለኛነት የሚታይባቸው፣ ወጣቶች የሚበዙበት ነው፤..... ከዚያ ዞን 5 ወሠዱት፤ ይህም በአብዛኛው ሽማግሌ ያለበት ዞን ሲሆን፣ በአንፃራዊ መልክ 100 ያህል እስረኞች የሚገኙበት ጥሩ እስር ቤት ሊባል ይቻላል፤ የእስር ቤቱ ኃላፊ ዎች ግን አሁንም ከዚህ አውጥተው ባዶ ክፍል ለብቻው ነው ያሠሩት፤ በዚያ ቃሊቲ ወህኒ ቤት ለብቻው የታሠረ እስረኛ እኔ አስከማውቀው ባለፈው ዓመት ማብቂያ ላይ የተገደሉት የቀድሞው የሕወሐት ታጋይና

የአቶ ክንፈ ገ/መድህን ገዳይ የተባሉት ሻለቃ ፀሐዬ ወ/ስላሴ ነበሩ፤... ይህ ሁሉ ስለ ሐገሩ፣ስለወገኑ የሚያዜመውን፣ ለፍቅር እንጂ ለጥላቻ ስፍራ የሌለውን ወጣት ለማሸበር እና አንገቱን እንዲያቀረቅር ለማድ ረገ ያለመ መሆኑ ከቶም የሚያጠራጥር አይደለም፤ይህ የጥላቻ ጉዞ ለሁላችንም አይጠቅምም።

.... ፅሁፌን ለማጠቃለል የቴዲን ጉዳይ ከሕግ የበላይነት ጋር በማያያዝ ስለርሡ የሚቀረቀር ወገኖችን ለማጣጣል የሚደረገውን የገዢዎች ሰፈር ጫጫታ በተመለከተ አንድ ነገር ላንሳ፤ የሕግ በላይነት በኢትዮጵያ የለም እንጂ፣ቢኖርማ ኖሮ በዚህ ላይ ከማንም በላይ ተጠቃሚው ተራው ዜጋ በሆነ ነበር፣.. በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት በኖረ ኖሮ... ፖለቲካዊ ጉዳዮችን እንተውና፣ የአባ ፈቃደ ስላሴ ገዳይ የታለ ፍ/ቤት የቀ ረበው? አባ ፈቃደ ስላሴ ጥር 17/89 በአደባባይ ሕዝብ በተሠበሠበበተ በጥይት እንደተገደሉና የገደለውም ማን እንደሆነ እየታወቀ፣ይኸው 11 ዓመት መች ፍ/ቤት ቀረበ? ... ከሩቅ ወደ ቅርብ ስንመጣ ጥቅምት 23/98 አንዲት አርጩሜ እንኳን በእጁ ላይ ያልነበረን ወጣት መሽታ ቤት በጥይት ደብድቦ የገደለ የኢህአዴግ አባል በ2ሺ.ህ ብር ዋስትና ሲፈታ እኮ የአይን ምስክር ነን።

Kunoweliso2000@yahoo.com